የኅብረተሰብኣዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ፤

የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ፤

# የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ።

## PROVISIONAL MILITARY GOVERNMENT OF SOCIALIST ETHIOPIA

## MINISTRY OF TRANSPORT & COMMUNICATIONS

# ETHIOPIAN POSTAL SERVICE



**የመጀመሪያው የቴሌፎን መስመር የተዘረጋበት ፻ኛ ዓመት**

**Centenary of the First Telephone Transmission**

**መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.**

**March 10, 1976**

## የመጀመሪያው የቴሌፎን መስመር የተዘረጋበት ፻ኛ ዓመት

በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ፤ የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ፤ ለመጀመሪያው የቴሌፎን መስመር ለተዘረጋበት ፻ኛ ዓመት መታሰቢያ ሦስት ዓይነት ቴምብሮች አሳትሞ ከመጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. የሚያወጣ መሆኑን ያስታውቃል ።

የቴምብሮቹ ሥዕል የተዘጋጀው በአቶ ወርቁ ካሣ ሲሆን ቴምብሮቹ በፎቶ አፍሴት የተሠሩ ሆነው በአምስት ቀለማት የተዋቡ ናቸው ። ቴምብሮቹን ያተመው አስፒዮቲ ኤልካ የሚባለው የግሪክ ኩባንያ ነው ። የእያንዳንዳቸውም መጠን ከነጠርዙ 26 X 36.5 ሚሊ ሜትር ሆኖ ዋጋቸው በኢት. $0.30. $0.60 እና $0.90 ነው ።

የእያንዳንዱ ዓይነት ቴምብር ብዛት 60,000 ነው ። ከዚህም በቀር ቴምብሮቹ ለሺያጭ በሚወጡበት ዕለት ብቻ የሚሸጥ ለነዚሁ ቴምብሮች መለጠፊያ የሚሆን ዋጋው በኢት $0.20 የሆነ የመጀመሪያ ቀን ኤንቬሎፕ ስለተዘጋጀ ለመግዛት የሚፈልጉ ሁሉ አዲስ አበባ ፤ ከሚገኘው ከፊላቴሊ ክፍላችን ፤ አሥመራ ፤ ፍቼ ፤ አሰብ ፤ ከረን ፤ ደቀመሃሪ ፤ ጊንዳዕ ፤ አዲግራት ፤ አርባ ምንጭ ፤ አሰላ ፤ ደምቢዶሎ ፤ አክሱም ፤ አዋሳ ፤ ድሬዳዋ ፤ ደብረብርሃን ፤ ደብረዘይት ፤ ደብረ ማርቆስ ፤ ሻሸመኔ ፤ ዲላ ፤ ነገሌ ቦረና ፤ ደሴ ፤ ጐሬ ፤ባሕርዳር፤ ጐንደር ፤ ጋምቤላ ፤ ጅማ ፤ ወላሞ ሶዶ ፤ ይርጋዓለም ፤ ጐባ ፤ ሐረር ፤ ለቀምት ፤ መቀሌ ፤ ምጽዋ ፤ ናዝሬትና ጅጅጋ ፖስታ ቤቶች ለመግዛት የሚቻል መሆኑን እያስታወቅን ፤ ቴምብሮቹ ግን በኢትዮጵያ ፖስታ ቤቶች ሁሉ ከመጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ጀምሮ የሚሸጡ መሆናቸውን እንገልጻለን ።

የፖስታ አገልግሎት ድርጅት ፤

## አለክሳንደር ግራሀም ቤል (እ.ኤ.አ. ፲፰፻፵፯-፲፱፻፳፪) :—

አለክሳንደር ግራሀም ቤል የተባሉት የቴሌፎን ፈላስፋ በእስኮትላንድ ሀገር በኢድንበርግ ከተማ እ.ኤ.አ. መጋቢት ፫ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም. ተወለዱ።ትምህርታቸውንም ያጠናቀቁት በኢድንበርግና በሎንዶን ዩኒቨርሲቲ ሲሆን በጤናቸው መታወክ ምክንያት እ.ኤ.አ. ፲፰፻፸ ዓ.ም. ከአባታቸው ጋር ወደ ካናዳ ተሰደዱ ። እ.ኤ.አ. በ፲፰፻፸፪ ዓ.ም. ቦስተን ከተማ የዲዳዎች መምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ከመክፈታቸውም በላይ በንግግር ሥልት መምሪያ አሰጣጥ በኩልም ራሳቸው ሲሳተፉ ቆይተዋል።እ.ኤ.አ. በ፲፰፻፸፫ ዓ.ም. በቦስተን ዩኒቨርሲቲ የድምጽ ቃና ዘይቤ ፕሮፌሰር ሆኑ ። እ.ኤ.አ. በ፲፰፻፸፮ ዓ.ም. የምርመራቸውን ፍሬ ባጠቃላይ የሚያሳይ መሣሪያ በኤግዚቢት መልክ አሳዩ።ይኸውም መሣሪያ ድምጽ በኤሌክትሪክ ኃይል እንዴት እንደሚጓዝ የሚያሳይ ሲሆን በመጠኑ ተደክሞበትና ተሻሽሎ የአሁኑን ቴሌፎን የሚያበስር ነበር ። ከዚሁ ጋር የተያያዙ በዛ ያሉ መሣሪያዎችን እኚሁ ሰው በተለያዩ ጊዜ የፈለሰፉ ናቸው ። ቤል የዲዳዎች የንግግር ትምህርት የሚበለጽግበትን መንገድ የሚያደራጀው «የአሜሪካን ማኅበርና» እንዲሁም በቮልታ የሚገኘውን የዲዳዎች ዕውቀት መበልጸጊያ ጽ/ቤት መሥራች ነበሩ ። እርሳቸውም እ.ኤ.አ. በ፲፰፻፺፰ ዓ.ም. ለቅርብ ጊዜም ቢሆን የብሔራዊው የጂኦግራፊ ማኅበር ፕሬዚዳንትና የስሚዞንያን ድርጅት ተጠባባቂ ሆነው አገልግለዋል ። እ.ኤ.አ. ነሐሴ ፪ ቀን ፲፱፻፳፪ እኚሁ ታላቅ ሰው በመኖሪያቸው አካባቢ በኖቫ ስኮሺያ በባዴክ አቅራቢያ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም ሥራቸው ታሪካቸውን ሲያስታውሰው እንደ ሚኖር ግልጽ ነው ።

## ALEXANDER GRAHAM BELL (1847-1922)

U.S. inventor and physicist, inventor of the telephone, was born in Edinburgh, Scotland, on March 3, 1847. He was educated at Edinburgh University and the University of London, and because of illhealth, moved with his father to Canada in 1870. In 1872 he opened a School in Boston for training teachers of the deaf and also gave instruction in the mechanics of speech. The following year he became professor of vocal physiology in Boston University. In 1876 he exhibited an apparatus embodying the results of his studies in the transmission of sound by electricity, and this invention, with improvements and modifications, constitutes the modern telephone. He was also the inventor of the photophone, an instrument for transmitting sound by vibration in a beam of light, and of photographic apparatus. Later, he interested himself in the problem of mechanical flight. He gave numerous addresses and published many scientific monographs. Bell was the founder of the American Association to Promote the Teaching of Speech to the Deaf, and of the Volta Bureau for the increase in knowledge relating to the deaf. He was for a time President of the National Geographic Society and was appointed a regent of the Smithonian Institution in 1898. He died on August 2, 1922, at his summer home near Baddeck, Nova Scotia.

## DETAILS OF STAMPS

| | |
|---|---|
| Denominations | : Eth.$0.30,$0.60 and $0.90 |
| Size | : 26x36.5mms (including perforation) |
| Quantity | : 60,000 sets |
| Designer | : Worku Kassa |
| Printers | : Aspioti Elka, Graphic Arts Inc. Athens, Greece |
| First Day Covers | : 20 cents each |
| Process of Printing | : Offset |

First Day Covers are available at Addis Ababa, Asmara, Keren, Deke Mehari, Ghinda, Adigrat, Arba Minch, Assab, Assela, Awassa, Axum, Bahr Dar, Debre Marcos, Debre Berhan, Debre Zeit, Dembi Dolo, Dire Dawa, Dessie, Nekemptie, Dilla, Goba, Gambella, Gonder, Gore, Harrer, Jijiga, Jimma, Mekele, Massawa, Fiche, Nazareth, Negelle Borena, Shashemene, Wellamo Sodo and Yirgalem post offices, only on the day of issue.







Orders for stamps and F.D.Cs (in advance payment), to the Ethiopian Postal Service, Philatelic Section, Post Box 1112, Addis Ababa, Ethiopia, or to Philatelic Agencies of the Ethiopian Provisional Military Government, Les Editions Rodan, Ch. de Waterloo Stwg. 868/870, 1180 Brussels, Belgium, for Europe, British Isles and the Commonwealth or Stamp Values, P.O.Box 4107, Grand Central Post Office, New York City, N.Y. 10017, U.S.A. for North, Central and South America.

Ethiopian Postal Service

ንግድ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ።
CPP
ADDIS ABABA
COMMERCIAL PRINTING PRESS